# የጤና ሁኔታ በአሌክሳንድሪያ

**የአሌክሳንድሪያ ጤና ቢሮ ከሰኔ 2024 እስክ ሰኔ 2025 ባለው ጊዜ ሰፊ የማህበረሰብ ጤና የዳሰሳ ጥናት አካሂዶ ነበር። ውጤቱም በነዋሪዎቻችን መካከል ጤናን በሚመለከት ሰፊ ልዩነቶች እንዳሉ አስገንዝቦናል።**

ወደዚህ ደረጃ የደረስነው በአንድ ጀምበር አይደለም። የጤናችን ሁኔታ ለአስርት ዓመታት የዘለቁ ፖሊሲዎች፣ ሥርዓቶች/ተቋማት፣ ፕሮግራሞች እና እርምጃዎች ድምር ውጤት ነው። እነዚህ በአብዛኛው በዘረኝነትና *አድልዎ ላይ የተመሠረቱ ፖሊሲዎችና ሥርዓቶች አሁንም ድረስ አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች፣ አገልግሎቶች እና ከባቢዎች ተደራሽነት ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ። በመሆኑም በማህበረሰባችን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የህብረተስብ ክፍሎች የተለያየ የጤና ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።

የዳሰሳ ጥናቱ ውጤቶችን እንደ አመላካች በመጠቀም የአሌክሳንድሪያ ጤና ቢሮ እና አጋርነት ለጤናማ አሌክሳንድሪያ (Partnership for a Healthier Alexandria) የማህበረሰብ ጤና ማሻሻያ እቅድን (Community Health Improvement Plan) በማቀላጠፍ ከተማችንን ያግዛሉ። በሚቀጥሉት አምስት ዓመታትም ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮችን በጋራ በመለየት፣ ተግባራዊና በማህበረሰቡ ተሳትፎ የሚቀረጹ ስትራቴጂዎች ላይ ውይይት እናደርጋለን። ይህን መንገድ በመጠቀም ለሁሉም ጤናማ የሆነች አሌክሳንድሪያን እውን ለማድረግ ማህበረሰባችን ባጠቃላይ በተግባር ላይ እንዲረባረብ ማድረግ ይቻላል። እርስዎም እንዴት መሳተፍ እንድሚችሉ ለመረዳት www.tinyurl.com/ALXCHA24 ይጎብኙ!

*ይህም በርካታ የተለያዩ ዓይነት አድሎዎችን፣ ማለትም እድሜን፣ የአካል ጉዳትን፣ ጾታን እና የመሳሰሉ ሁኔታዎችን መሠረት ያደረጉ አድሎዎችን የሚያካትት ነው።

ሙሉውን የ2025 የጤና ሁኔታ ሪፖርታችን ይመልከቱ!

## ምን አከናወን

- ከ200 በላይ አሃዛዊ አመላካቾችን በመተንተን፣ የሥነ ህዝብና ጂኦግራፊያዊ ዝርዝሮችን የያዙ ምንጮችን አፈላልገናል።
- በከተማ አቀፍ የዳሰሳ ጥናቱ የማህበረሰብ አባላትን ዋነኛ የጤና ጉዳዮቻችን፣ የማህበረሰቡ ጥንካሪዎች እና መሻሻል የሚችሉ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ ጠይቀናል። የመላሾች የሥነ ህዝብ/የማንነት ስብጥር ከከተማው አጥቃላይ የህዝብ ስብጥር ጋር ተመሳሳይ ነው።
- አካባቢያዊ የእግር ጉዞ ወጎችን ከማካሄድ በተጨማሪ ከተማ አቀፍ የማህብረሰብ የፎቶ ስብስብ/አልበም አዘጋጅተን የእለት ተለት ጤና እና ደህንነት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ ከነዋሪዎች በቀጥታ ሰምተናል።

## ዋናዋና የዳሰሳ ጥናቱ ውጤቶች

### በማህበረሰብዎ ውስጥ ትልልቆቹ የጤና ጉዳዮች ምንድ'ናቸው?

| | |
|---|---|
| የአዕምሮ ጤና | 47% |
| መጠጥ፣ አደንዛዥ እጽ፣ ኦፒዬት መጠቀም | 30% |
| ከመጠን ያለፈ ውፍረት፣ አካላዊ እንቅስቃሴ እና የተመጣጠነ ምግብ | 26% |

### የማህበረሰብዎን የጤና ሁኔታ ምን ሊያሻሽለው ይችላል?

| | |
|---|---|
| አስተማማኝ፣ ጤናማ እና ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው የመኖሪያ ቤት | 43% |
| ለህጻናት፣ ወጣቶችና ለቤተሰብ ድጋፍ ማቅረብ | 25% |
| የአዕምሮ ጤና እና የአደንዛዥ እጽ መጠቀምን የሚመለከት አገልግሎት ተደራሽነት | 25% |

### የማህበረሰብዎ ዋነኛ ጠንካራ ጎኖች ምንድ'ናቸው?

| | |
|---|---|
| የማህበረሰቡ ብዝሃነት | 37% |
| በማህበረሰቡ የመሳተፍ እድሎች እና የእኔንት ስሜት | 30% |
| የትምህርት እድሎች | 28% |

# የተገነዘብነው ነገር

**የማህበረሰብ ሁኔታዎች እና መድሕን/ኢንሹራንስ**

- አማካይ ዓመታዊ ገቢ በ20% ጨምሮ $113, 600 ደርሷል። ነገርግን ከ12 አሌክሳንድሪያውያን አንዱ በድህነት ውስጥ ይኖራሉ። በአርላንድሪያ እና በአንዳንድ የዌስት ኤንድ አካባቢዎች ደግሞ ከ5 አሌክሳንድሪያውያን አንዱ በድህነት ውስጥ ይኖራሉ።
- የእግር ጉዞ ወግ ተሳታፊዎች እንደገለጹት፣ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የላንድማርክ እና የፓርከር ግሬይ/ብራደክ ሜትሮ አካባቢዎች ወጥ ያልሆነ የመሠረተ ልማት አቅርቦት/ጥገና እና ጥራት እንዲሁም ለአደጋ የሚያጋልጡ የእግረኞች መንቀሳቀሻዎችን ተመልክተዋል።
- 13% ህጻናት የምግብ ዋስትና የሌላቸው ሲሆን፣ ይህም በ2019 ከነበረው 11% በትንሹ ጭማሪ አሳይቷል። ከ4 ጥቁር ህጻናት ውስጥ አንዱ የምግብ ዋስትና የሌላቸው ሲሆን፣ ይህም በነጭ ህጻናት ካለው በ4 እጥፍ ከፍ ያለ ነው።

**የአኗኗር ዘዬ እና የጤና ነክ ጉዳዮች ተደራሽነት**

- በአርላንድሪያ፣ ቡረጋርድ እና ላንድማርክ አካባቢ ከ4 አዋቂዎች አንዱ በትርፍ ሰዓታቸው አካላዊ እንቅስቃሴ አያደርጉም።
- ከ4 አሌክሳንድሪያውያን ሦስቱ ባለፈው አንድ ዓመት ወደ ጥርስ ሃኪም ወይም ክሊኒክ ሄደዋል። አርላንድሪያ፣ ቡረጋርድ እና ላንድማርክ አካባቢዎች በዚህ ረገድ ከሌሎች አካባቢዎች በጣም ያንሳሉ።
- የወጣቶች የአደጋ ተጋላጭነት ባህሪ የዳሰሳ ጥናት ምላሽ ሰጪዎች እንደገለጹት ድብድብ፣ መሳሪያ መያዝ እና የኦንላይን ማሸማቀቅ (electronic bullying) ጨምሮ አብዛኛው ዓይነት የት/ት ቤት ብጥብጦች መጠን ከ2019 የማህበረሰብ ዳሰሳ ጥናት በኋላ ቀንሰዋል።

**የጤና ውጤቶች**

- በጥቁር እና ሌሎች ዘር ያላቸው አሌክሳንድሪያውያን መካከል በህይወት የመቆየት አማካይን በተመለከተ ከ 7 እስከ 9 ዓመት የሚመደርስ ልዩነት አለ።
- የአርላንድሪያና ላንድማርክ አካባቢዎች ነዋሪዎች ከፍተኛ ከመጠን ያለፈ ውፍረት መጠን የሚታይባቸው ሲሆን፣ ዝቅተኛ ደረጃ የአዕምሮና ጤና እና የአፍ/የጥርስ ጤና ሁኔታም አላቸው።
- በአሌክሳንድሪያ የልጃገረዶች እርግዝና እና የተለያዩ በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች (STIs) መጠን በቨርጂኒያ አጠቃላይና በሰሜን ቨርጂኒያ ካለው መጠን ከፍ ያለ ነው።
- በአሌክሳንድሪያ ከጉዳት/ከመቁሰል ጋር የተያያዘ የሞት መጠን (ከ100,000 ሰው 46.9) በቨርጂኒያ ግዛት ካለው መጠን (82.9) በግማሽ አካባቢ ያነሰ ሲሆን በ2019 ከነበረው (43.3) ግን በጥቂቱ ጨምሯል።

## ሪፖርቱን እንዴት ልንጠቀምበት እንችላለን?


**የከተማ አስተዳደር ተቋማት:** በእድሜ፣ በዘር/ብሄር እና በአካባቢ የተደራጀ አሃዛዊ መረጃ ፕሮግራሞችን/እቅዶችን በጣም በሚያስፈልጉበት ቦታ እንዲያተኩሩ ለማድረግና ለፕሮግራም ልኬቶች የመነሻ መስመር/መመዘኛ ለማዘጋጀት እንዴት ሊረዳ ይችላል?

**የማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች:** አሃዛዊ መረጃና የጤና ጉዳይ ግኝቶች እንዴት የእርዳታ ማጽደቅ፣ ሪፖርት ማዘጋጀትና እስትራቴጂካዊ እቅድ የማዘጋጀት ሥራዎችዎን ሊያጠናክሩ ይችላሉ?


**በህዝብ የተመረጡ ባለሥልጣናት/የከተማው መሪዎች:** የማህበረሰብ ጤና የዳሰሳ ጥናቱ ግኝቶች/ውጤቶች የአቅርቦት/የሃብት ምደባን፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ለመለየት እና አሁን ላለው ሁኔታ ምክንያቶቹን ከሥረ መሠረቱ ለመመርመር እንዴት መነሻ ሊሆን ይችላል?

**የማህበረሰብ አባላት፣ የእምነት ስብስቦች እና የንግድ ተቋማት:** ከተለዩት ችግሮች ውስጥ በየትኞቹ ላይ ልትሰሩ ትፈልጋላቹ? ምን እንዲሻሻል ልታግዙ ትችላላቹ?

**ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ አዋቂዎች በመቶኛ፣ 2019-2023**




**በሞቃት ቀናት የመሬት ውጪያዊ የሙቀት መጠን፣ 2020 - 2021**



**ጥርሳቸው ሙሉበሙሉ የወለቀ/የረገፈ እድሜያቸው ከ65 በላይ የሆኑ አዋቂዎች በመቶኛ፣ 2022**

